ቀን :- ሚያዝያ 27 2014 ዓ.ም

ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ | ማብራሪያ

በሀገራችን የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ ሁለት ዓይነት የታክስ አወቃቀሮች ያሉ ሲሆን እነዚህም ቀጥታ የሆኑ ታክሶች እና ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች በመባል ይታወቃሉ። ቀጥታ ባልሆኑ ታክሶች ማዕቀፍ ውስጥ ከሚካተቱት ታክሶች መካከል **የተጨማሪ እሴት ታክስ** እና **የተርን ኦቨር ታክስ** በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህ ሁለቱም የታክስ ዓይነቶች ቀጥታ ያልሆኑ የታክስ ዓይነቶች በመሆናቸው እና ተመሳሳይ በሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የሚጣሉ በመሆናቸው ለታክሶቹ ዓላማ፣ አንድነትና ልዩነት ላይ የተጣራ ግንዛቤ ባለመኖሩ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች የሚነሱ በመሆኑ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ይህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ አዘጋጅቻለሁ ::

VAT

የተጨማሪ እሴት ታክስ /value added tax/ (VAT) መሠረቱ ሰፊ የሆነ በፍጆታ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ወይም በተጠቃሚው ወጪ ላይ ተመስርቶ የሚጣል ታክስ ሲሆን የሚሰበሰበውም በምርት ማምረት፣ ማከፋፈልና በስርጭት ሂደት ውስጥ በሚፈጠረው እሴት እና በአገልግሎት ወቅት በተጨመረው እሴት ላይ ሆኖ ምርቱ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ወይም ማንኛውም ታክሱ የሚከፈልበት ዕቃ እና አገልግሎት ግብይት ሲፈጸም ነው።

TOT

በሌላ በኩል የተርን ኦቨር ታክስ /Turn Over Tax/ (TOT) በአገር ውስጥ በሚከናወን የዕቃ ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ወቅት የአቅርቦት ሰንሰለቱን ተከትሎ በየደረጃው የሚጣል ቀጥተኛ ያልሆነ የታክስ ዓይነት ነው።

ይህ ታክስ ቀደም ሲል የነበረው የሽያጭ ታክስ በተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲተካ ሲደረግ በንግድ ግንኙነት ውስጥ ሊፈጠር የሚችለዉን የንግድ ሚዛን መዛባት በማስወገድ፤ ፍትኃዊነትን በማስፈን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ግዴታቸዉን እንዲወጡ የማስተካከያ / የማካካሻ ታክስ መጣል በማስፈለጉ እንዲሁም የታክስ ስርዓቱን ሽፋን የተሟላ በማድረግ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማፋጠን ሲባል የተጣለ ታክስ ነዉ።

የታክሶቹ ተመሳሳይነት

1. የተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ የተርን ኦቨር ታክስ በቀጥታ ከግብር/ ታክስ ከፋዩ ካዝና / ቋት ወይም ሰርቶ ካገኘዉ ገቢ የሚከፈሉ ሳይሆን በመንግስት ዉክልና በተሰጠዉ መሠረት ታክስ ከፋዮች ከተጠቃሚዉ ህብረተሰብ የሚሰበሰቡ በመሆናቸዉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ከሚባሉት ይመደባሉ።

2. ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሁለቱም የታክስ አይነቶች በተጠቃሚዉ የፍጆታ ወጪ ላይ ተመስርተዉ የሚጣሉ የታክስ ዓይነቶች ናቸዉ። ይህም ባህሪያቸዉ የሽያጭ ታክስን ተክተዉ ከመምጣታቸዉ ጋር የሚመነጭ ነዉ።

3. ሁለቱም የታክስ ዓይነቶች በመተካካት ወይንም አንዱ በሌለበት ሌላኛዉ ከመምጣቱ ጋር ተቆራኝተዉ በመሠረታዊ ፍላጎትነት ከሚፈረጁ ግብይቶች ላይ ባለመጣላቸዉም ይመሳሰላሉ። (ለህብረተሰቡ መሠረታዊ የሚባሉትን ግብይቶች ከታክሱ ነጻ ናቸዉ)

   ይህም ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ ሆነ ግብይት ከተርን ኦቨር ታክስም በተመሳሳይ መንገድ ነጻ ሆኖ ተደንግጎ ይገኛል። መሰረታዊ ፍላጎታችንን ከታክሱ ነጻ በማድረግ የዋጋ ተመጣጣኝነትን ከማረጋገጥ ባለፈ የሁለቱም ታክሶች በተመሳሳይ ግብይቶች ላይ ያለመጣል ለታክስ አስተዳደሩ አመቺነትም ጉልህ ሚና አለዉ ለማለት ያስችላል።

Mobile: +251 911 190 299
E-mail: lawyer@samuelgirma.com
Addis Ababa, Ethiopia

ለምሳሌ ያህል የሚከተሉት አገልግሎቶችና ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ ከተርን ኦቨር ታክስ መረብ ነጻ ናቸዉ

እነዚህም፡-

■ ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና መኖሪያ ቤት ኪራይ፣

■ የፋይናንስ አገልግሎት፣

■ለሳንትሞች እና ለሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚዉሉት በስተቀር የአገር ዉስጥ እና የዉጭ ሀገር ገንዘቦች እና የዋስትና ሠነዶችን፤

■ በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮ ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣

■ በሕክምና አገልግሎት እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ መሠረት በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች፣

■ በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማሰተማር አገልግሎቶች፣ እንዲሁም ለሕፃናት ጥበቃ በመዋዕለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

■ በሰብአዊ እርዳታ የሚዉሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች

■ የኤሌክትሪክ የኪሮሲን እና የውሃ አገልግሎት፣

■ በማናቸውም የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግስት የሚከፈል ክፍያ ይገኙበታል።

■ በማናቸውም ደረጃ የሚቀርቡ የምግብ እህሎችና ጥራ ጥሬዎች (ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ሩዝ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ሽንብራ፣ ዳጉሳ፣ ቦቆሎ፣ ማሽላና የመሳሰሉት) በጥሬ ወይም በዱቄት መልክ ግብይት ሲካሄድ ሁለቱንም የታክስ ዓይነቶች የማስተዳደር፤ ሪፖርት የማቅረብ እና በህግ በተቀመጠዉ ጊዜ የመክፈል ግዴታ የተጣለዉ ዕቃዎቹን ወይም አገልግሎቶቹን በሚሸጠዉ ሰዉ ላይ ነዉ።

4. የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ተመሳሳይነት በህግ ማዕቀፎቹ ላይ በግልጽ ሚስተዋልባቸዉ ድንጋጌዎች በርካታ ናቸዉ። ሁለቱን ታክሶች በሚጥሉት አዋጆች ላይ ታክስን በግዜ ባለማሳወቅ የሚጣለዉ አስተዳደራዊ መቀጫ እና አዘግይቶ በመክፈል የሚታሰበዉ ወለድ ተመሳሳይ ናቸዉ። ከዚህ ፍትሐብሔራዊ ቅጣት በተመሳሳይ ሁለቱን ታክሶች በሚገዙት የህግ ማዕቀፎች ዉስጥ የተደነገጉት የወንጀል ጥፋቶች እና ለጥፋቶቹ የተቀመጡ ቅጣቶች ተመሳሳይ ናቸዉ።

የታክሶቹ ልዩነት

1. የታክሶቹን አጣጣል ተከትለዉ የተጨማሪ እሴት የሚጣለዉ በምርት ወይም በአቅርቦት ላይ በሚጨመረዉ እሴት ላይ ሲሆን የተርን ኦቨር ታክስ የሚጣለዉ ግን የአቅርቦት ሰንሰለቱን ተከትሎ ነዉ። በሌላ አገላለጽ የተጨማሪ እሴት ታክስ በምርት ሂደት ወይም በአቅርቦት ሰንሰለት ቀድሞ የተከፈለን የግብዓት ታክስ የማቀናነስ ሂደትን የሚከተል ሲሆን በተርን ኦቨር ታክስ ግን አጠቃላይ የሽያጭ ዋጋዉ ላይ እየተከተለ ቀድሞ የተከፈለን ታክስ ሳያቀናንስ ተሰልቶ ይሰበሰባል።

ተጨማሪ እሴት ታክስ የታክስ ተቀናናሽ ስሌት ሲኖረዉ ተርን ኦቨር ታክስ ግን የተንከባላይነት (cascading effect) የሚንጸባረቅበት ነዉ።

2. የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ልዩነታቸዉ በመጣኔያቸዉም ጎልቶ ይንጸባረቃል። የተጨማሪ እሴት ታክስ በመሪህ ደረጃ አገልግሎትን እና የዕቃን አቅርቦትን ሳይለይ አስራ አምስት በመቶ (15%) ታክስ እንዲሰበሰብበት ምጣኔ (rate) የተቀመጠለት ሲሆን የዉጪ ንግድን ለማበረታታት በዜሮ ምጣኔ (zero rate) ታክሱ የሚጣልባቸዉን አቅርቦቶችን አስቀምጧል።

የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰላበትን ሂደት የበለጠ ለማብራራት የሚከተለዉን **ምሳሌ እንመልከት፤**

ነዋሪነቱ በሃዋሳ ከተማ የሆነ አንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ታክስ ከፋይ ከአዲስ አበባ አንድ የ100 ብር ዋጋ ያለዉ ዕቃ የተ.እ.ታክስን ጨምሮ በ115 ብር ቢገዛና ወደ ሀዋሳ ለማድረስ 20 ብር የትራንስፖርት ወጪ ቢከፍል እንዲሁም

እቃዉን በሀዋሳ ገበያ ሲሸጥ 15 ብር የትርፍ ሂዳግ እና 15% የሽያጭ ታክስን ጨምሮ ቢሸጠዉ ሀዋሳ ላይ ከተጠቃሚዉ መሰብሰብ ያለበት የተ.እ.ታክስ እና ከዚሁ ዉስጥ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ያለበት የታክስ መጠን በሚከተለዉ ሁኔታ ይሰላል።

በአዲስ አበባ የዕቃዉ ዋጋ (የተ.እ.ታክስን ሳይጨምር) = 100

በአዲስ አበባ የተከፈለ የተ.እ.ታክስ = 100× 15% = 15 ብር

በአ.አ ለዕቃዉ የተከፈለ ጠቅላላ ዋጋ (የተ.እ.ታክስን ጨምሮ) = 115 ብር

ዕቃዉ ወደ ሀዋሳ ሲደርስ የትራንስፖርት 20 ብር እና የግብር ከፋዩን ትርፍ 15 ብር ጨምሮ ....= 115 +20+ 15 = 150 ብር

ሀዋሳ ላይ የዕቃዉ ዋጋ አ.አ የተከፈለዉን የተ.እ.ታክስ ሳይጨምር = 135 (150-15ብር)

ሃዋሳ ላይ መሰብሰብ ያለበት የተ.እ.ታክስ ….= 135 ×15% = 20.25

ለመንግስት ገቢ መደረግ ያለበት የተ.እ.ታክስ መጠን (ሀዋሳ የተሰበሰበዉ ታክስ ሲቀነስ አ.አ የተከፈለዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ) 20.25-15 = 5.25 ነዉ።

ከዚህ መረዳት ሚቻለዉ ሀዋሳ ላይ ያለዉ አቅራቢ ከሰበሰበዉ የተጨማሪ እሴት ታክስ ዉስጥ አ.አ. የከፈለዉን ለራሱ በማስቀረት ለመንግስት ገቢ ማድረግ የሚጠበቅበት በልዩነት የሰበሰበዉን ብቻ ነዉ።

ይህም የተ.እ.ታክስ ምርት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚተላለፍበት ወቅት በሚፈጠር የታክስ ተንከባላይነት ባህሪይ ቀደም ብሎ የተከፈለዉን ታክስ በማቀናነስ በታክስ ላይ ታክስ የማሰብ ሁኔታ (Cas- cading Effect) እንዳይፈጠር የሚያደርግ መሆኑን ያሳያል።

3. በሌላ በኩል የተርን ኦቨር ታክስ አገልግሎትንና ዕቃን በተለያየ መጣኔ የሚያሳይ የታክስ አይነት ነዉ። ለአገልግሎት የተደነገገዉ የተርን ኦቨር ታክስ ምጣኔ አስር በመቶ (10%) ሲሆን ለዕቃ ሽያጭ ደግሞ ምጣኔዉ ሁለት በመቶ (2%) ነዉ። ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው። የጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ማለት የወጪ ተቀናሽ ሳደረግ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ሲሆን የተሸጡ ዕቃዎች የተመረቱበትን ወይንም የተገዙበትን ዋጋ ይጨምራል።

ለምሳሌ ያህል አንድን ዕቃ ተርን ኦቨር ታክስን ጨምሮ በ1000 ብር የሸጠ ማንኛዉም ታክስ ከፋይ ከሸማቹ የሚሰበስበዉ የተ.እ.ታክስ ልክ

1000×2%= 20ብር የተርን ኦቨር ታክስ ልክ ይሆናል ማለት ነዉ።

አገልግሎት ላይ ቢሆን ግን በ10 በመቶ ነዉ የሚሰላዉ።

4. የተጨማሪ ታክስን ለመሰብሰብ ተመዝጋቢ መሆን ሲያስፈልግ የተርን ኦቨር ታክስን ለመሰብሰብ ግን የተለየ ምዝገባ ሳያስፈልገዉ በግብር ከፋይነት ተመዝግቦ በንግድ ስራ ላይ መሠማራት እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ያለመመዝገብ በቂ ነዉ።

ሳሙኤል ግርማ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ
+251-911-190-299

Website https://samuelgirma.com

Facebook https://fb.me/tebekasamuel

Telegram https://t.me/tebekasamuel
https://t.me/lawyersamuel
https://t.me/tebeka

Protect pdf from copying with Online-PDF-No-Copy.com